## የዓመቱ የሥራ ዕድል ፈጠራ ሥራ ያለበት ደረጃ፡

በክልላችን የከተሞች ልማት ፈጣን እንዲሆን የገጠር ልማትን መሠረት በማድረግ የከተማና ገጠርን እንዲሁም የከተማና ከተማን ትስስር በማጠናከር የገበያ፣ የአገልግሎት እና የኢንዱስትሪ ማዕከል እንዲሆኑ ስናደርግ በመሆኑ ይህን ለማሳካት ከሚያስችሉን ስራዎች መካከል የኢንተርፕራይዞች ልማትን የማስፋፋት እንቅስቃሴ በዋናነት ይጠቀሳል፡፡ በመሆኑም የክልሉ የንግድና ኢንዱስትሪ ሴክተር በነኚሁ ከተሞች የሚገኘውን ሰፊ የሰው ሃይል በተለይም ወጣቱንና ሴቶችን በመጠቀምና ወደ ስራ በማሰማራት ባለፉት አምስት ዓመታት በተቀናጀ አመራር ተግባራዊ ያደረገው ስራ ለበርካቶች የስራ ዕድልና የገቢ ምንጭ አስገኝቷል፡፡

ከዚህም ባለፈ ወደ መካከለኛ ባለሀብትነት የተቀየሩ 123 ማኀበራት ራሳቸውን ችለው እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ፡፡




**በቀረበላቸው የመረጃ አቅርቦት ድጋፍ መሠረት ውጤታማ**
**የሆኑ ማኀበራት ሥራዎች (ሀዋሳ)**

በቢሮው የኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ከተቋቋመ ጀምሮ የ10 ዓመት የልማት ፕሮግራም በማውጣት 420,000 የሚሆኑ ተጠቃሚዎችን ለመደገፍ ዕቅድ መያዙን የክልሉ ም/ር/መ/ር እና የቢሮው ኃላፊ አቶ ታገሠ ጫፎ የገለፁ ሲሆን አያይዘውም ባለፉት 5 ዓመታት ወደ 163,725 አንቀሳቃሾች በ13,702 ማኀበራት መደራጀታቸውን ገልፀው ቢሮው በተለይም በ2002 ዓ.ም በጀት ዓመት በያዘው ዕቅድ መሠረት ባለፉት ዘጠኝ ወራት ድህነትን ከመቅረፍ አኳያ ተገቢውን ስራ መስራቱን ገልፀዋል፡፡



**የተከበሩ አቶ ታገሠ ጫፎ የክልሉ ም/ር/መስተዳድርና**
**የንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ኃላፊ**

በቀጣይም ቢሮው የታዩ ማነቆዎችን ለመቅረፍ ይረዳው ዘንድ የአፈፃፀም ዕቅዱን በመገምገም የፈተሸ ሲሆን በገጠሩ የሚገኘውን ሰፊ የሰው ሃይል ወደ ስራ ለማሰማራትና የክልሉን ዕድገት ለማፋጠን እንዲቻል የ2003 ዓ.ም በጀት ዓመት ጀምሮ የስራ ዕድል ፈጠራ ስራ በከተማም በገጠርም ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ይከናወናል፡፡

## በኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የቴክኒክ ድጋፍ ለሚሠጡ ባለሙያዎች የክህሎት ክፍተት ማሟያ ሥልጠና ተሠጠ፡፡

በክልሉ ከሚገኙ ሃያ ሁለት ሪፎርም ከተሞች ለተውጣጡ 74 የቴክኒክ አማካሪዎች ከፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ሥራዎች ልማት ኤጀንሲ ጋር በመተባበር የክህሎት ክፍተት ማሟያ ሥልጠና ከግንቦት 23 2002 ዓ.ም ጀምሮ ለአስራ አምስት ቀናት ተሠጥቷል፡፡ ሥልጠናው ያተኮረው የቴክኒክ አማካሪዎች ለኢንተርፕራይዞች አገልግሎት በሚሠጡባቸው ሙያዎች ላይ ሲሆን በብረታ ብረትና እንጨት እና በጨርቃ ጨርቅና አልባሳት የሙያ ዘርፍ የተግባርና የቲዮሪ ሥልጠና እንዲሠጥ ተደርጓል፡፡



ሠልጣኞች በብረታ ብረትና ሽማ ስራ ስልጠና ላይ

42 ባለሙያዎች በብረታብረትና እንጨት 32 ባለሙያዎች ደግሞ በጨርቃ ጨርቅና አልባሳት የሰለጠኑ ሲሆኑ በዘርፉ ለተሠማሩ ኢንተርኘራይዞች የተሟላ ድጋፍ መስጠት ይችሉ ዘንድ በዋናነት ወቅታዊ የክህሎት ክፍተት በሚታይባቸው በጥሬ ዕቃና በማሽን አጠቃቀም እና በሾፕ ማኔጅመንት የቲዮሪና የተግባር ሥልጠና ያገኙ ሲሆን የተግባር ሥልጠናው በዎርክሾኘ ውስጥ ባሉ የተለያዩ መሣሪያዎች የተደገፈና በልብስ ስፌት የፓተርን ሥራና የሽመና ስራዎችን ጨምሮ እንዲሠለጥኑ ተደርጓል።

የኢንተርኘራይዞች ልማት ኤጀንሲ ሥራ አስኪያጅ አቶ ገ/መስቀል ጫላም በሥልጠናው የመዝጊያ ስነሥርአት ላይ ተገኝተው ለሥልጠናው ተሣታፊዎች ባደረጉት ንግግር በሥልጠናው ያገኙትን ዕውቀት በመጠቀም ለኢንተርኘራይዞች ተገቢውን ድጋፍ ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው አሳስበዋል። የሥልጠናው ውጤትም በኢንተርኘራይዞች የምርት ጥራትና ምርታማነት መጨመርና በገበያ ላይ ብቁ ተወዳዳሪ መሆንን እንደሚያረጋግጥ አክለው ገልጸዋል።

## ቀጣይ የኢንተርፐራይዞች የትኩረት አቅጣጫችን፡

ሀገራችን የምትከተለውን የዳበረ የነፃ ገበያ ግንባታ ሥርዓት መሠረት ያደረጉ የከተማ ልማት ፖሊሲ የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂና የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲዎች ተዘጋጅተው በሀገር አቀፍና

በክልላችን ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ በዚህም መሠረት የህዝቡን መሠረታዊ ፍላጎት ከማሟላት ባሻገር ዲሞክራሲንና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ይረዳ ዘንድ የከተሞች ኢንዱስትሪ ልማት ፓኬጅ ተቀርፆ የተለያዩ ፕሮግራሞች ተነድፈዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ አንዱ የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋም ነው፡፡

ይህን የልማት ፕሮግራም ስኬታማ ለማድረግ በመንግስት በኩል የተለያዩ ንዑሳን ፕሮግራሞች፣ ስኪሞች፣ ፓኬጆች፣ ማንዋሎችና መመሪያዎች ተዘጋጅተው ባለፉት ዓመታት ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡ በዚህም በክልላችን ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ ከፍተኛ ርብርብ በመደረጉ ለውጦች እየታዩ ነው፡፡ አዳዲስ ስራዎችን ከመፍጠርና ከማስፋፋት እንዲሁም ከማመቻቸት አንፃር የነበረውን ሂደት ወደ ኋላ መለስ ብለን ስንቃኝ በ1996 ዓ.ም በማይክሮ ኢንተርፕራይዝ አደረጃጀት በክልሉ ባሉ ሶስት ከተሞች /አርባ ምንጭ፣ ሀዋሳ፣ ሚዛን ተፈሪ/ 645 አባላት ባሉት 30 ማኅበራት ብቻ የተጀመረ ነበር፡፡

በአጠቃላይ ከ1997 እስከ2002 ዘጠኝ ወራት ድረስ በፓኬጅና መደበኛ 163,725 አባላት ያሉት 13,702 ማኅበራት ሊደራጁ ችለዋል፡፡ እነኚህም ዜጎች በተደረገላቸው የተመረጡና ሁሉ አቀፍ ድጋፎች ኑሮአቸው ከነበሩበት በተሻለ መልኩ የተለወጠ ሲሆን የተወሰኑትም ወደ መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ባለቤትነት ተሸጋግረው ለሌሎችም ስራ አጥ ወጣቶች የስራ ዕድል ፈጥረዋል፡፡

በ2003 በጀት ዓመት የኢንተርፕራይዞች ልማት ግብ የገጠርና ግብርና ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂን እውን ከማድረግ ጎን ለጎን ድህነትንና ስራ አጥነትን በከተሞች ብቻ ሳይሆን በገጠር ወረዳ ማዕከላት የሚታየውን ከፍተኛ የስራ አጥ ቁጥር ለመቀነስ የሚያስችል ስራ ይሰራል፡፡

ይህን የልማት አቅጣጫ እውን ማድረግ ይቻል ዘንድ የከተማውም ሆነ የገጠሩ ነዋሪ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን የማልማት፣ የመደገፍና የማስፋፋት ስራን አብሮን መስራት ይጠበቅበታል፡፡ እንዲሁም በየደረጃው ያለው አካል የሚጠበቅበትን የስራ ድርሻ በከፍተኛ የሃላፊነት ስሜትና ትኩረት ሊወጣ ይገባል፡፡



በቀጣይ የገጠር ወጣቶች ስራ አጥ አይሆኑም (አርባ ምንጭ አካባቢ)

## የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራዎችና የልማት ስራዎች፡

◆ **የማስፈፀም አቅም ግንባታን በተመለከተ፡**

በዘርፉ ልማት እንቅስቃሴ ዙሪያ በአመለካከት፣ በክህሎትና በግብአት አቅርቦት በኩል ያሉ ክፍተቶችን ለመሙላት ለአስፈፃሚ፣ ለፈፃሚ፣ ለባለሙያና ተባባሪ ወገኖች በድምሩ ለ543 ሠልጣኞች በከተማ ልማትና በኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ፣ በኢንተርፕራይዞች ልማት ፕሮግራምና የአፈፃፀም ማንዋሎች እንዲሁም በመሠረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ አፈፃፀም መመሪያና ቲም ቻርተር ዙሪያ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

ከክላስተር ጋር የተያያዙ ስራዎች በአግባቡ ተመርተው ውጤታማ እንዲሆኑ በዩኒዶና በፌደራል ጥቃቅንና አነስተኛ ልማት ትብብር ከክልልና ከተለያዩ የሪፎርም ከተሞች ለተውጣጡ 59 ባለሙያዎች እና የስራ ሂደት ኃላፊዎች ስልጠና የተሰጠ ሲሆን በኤጀንሲው አማካኝነት ከክልልና ከታችኛው መዋቅር ለተውጣጡ 160 ባለሙዎች በሆሣዕና ከተማ በመረጃ አሰባሰብ፣ አያያዝና አደረጃጀት ዙሪያ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡



የቴክኒክ አማካሪዎች ስልጠና ሲወስዱ (አ.አ.)

ከዚህ በተጨማሪ የአንድ ማዕከል አገልግሎትና የማማከር አገልግሎትን በሚመለከት ያጋጠሙ ችግሮችን ለመረዳት በክልሉ ወደሚገኙ የተለያዩ ከተሞች በመንቀሳቀስ ችግሮችን የመለየት ስራ ተሰርቷል፡፡ እንዲሁም መልካም ተሞክሮዎችን ወደ ሌሎች ለማስተላለፍ የሚያስችል የክትትልና የድጋፍ ስራ የተቀመጠ ሲሆን በዚሁ መሠረት በአሁኑ ወቅት በክልሉ በሚገኙ 45 ክፍለ-ከተሞች እና 70 ወረዳዎች የአንድ ማዕከል አገልግሎት እንዲሰጥ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

◆ **የልማት ሥራዎችን በተመለከተ፡**

**የአደረጃጀት ድጋፍ፡**

በ2002 በጀት ዓመት ባለፉት ዓመታት እንደተደረገው ሁሉ የተለያዩ ድጋፎች ተሰጥተዋል፡፡ በዚሁም አንቀሳቃሾች በአካባቢው የሚገኘውን ውስን ሀብት በመጠቀም በገበያ ላይ ብቁ ተወዳዳሪ እየሆኑ ይገኛሉ፡፡

በዚህ በጀት ዓመት ባለፉት ዘጠኝ ወራት በሁለቱ ፕሮግራሞች የሚከተለው የአፈፃፀም ውጤት ታይቷል፡፡ በፓኬጅ ፕሮግራም በጨርቃጨርቅና አልባሳት፣ በኮንስትራክሽን፣ በብረታብረትና እንጨት ስራ፣ በአግሮ-ፕሮሰሲንግ፣ በከተማ ግብርናና በውበትና ፅዳት መስኮች ወንድ 8,924 ሴት 9,476 በድምሩ 18,400 ተጠቃሚዎችን በ1,684 ማኅበራት ለማደራጀት ታቅዶ፣ ወንድ 10,710 ሴት 6,054 በድምሩ 16,764 አንቀሳቃሾችን በ1,402 ማኅበራት የተደራጁ ሲሆን ክንውኑም 91.1% ሆኗል፡፡ በመደበኛውም ፕሮግራም በንግድ፣ በአገልግሎትና በኢንዱስትሪ ወንድ 20,880 ሴት 9,825 በድምሩ 30,705 ተጠቃሚዎችን በ3,070 ማኅበራት ለማደራጀት ታቅዶ 14,091 ሴት 7,117 በድምሩ 21,211 ተጠቃሚዎችን በ1,879 ማኅበራት ለማደራጀት ተችሏል፡፡ ክንውኑም ከተያዘው ዕቅድ አንፃር 69.1% ሆኗል፡፡

### የስልጠና ድጋፍ፡

የተደራጁ አንቀሳቃሾችን በንግድ ስራ አመራር እና የቴክኒክና ሙያ ክህሎት ክፍተትን በማስወገድ በገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ በሁለቱም ፕሮግራሞች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በፓኬጅ ፕሮግራም ወንድ 21,125 ሴት 12,834 በድምሩ 39,959 ተጠቃሚዎችን በንግድ ስራ አመራር የሰለጠኑ ሲሆን የዕቅድ አፈፃፀም ክንውኑም 74.1% ነው፡፡ በቴክኒክና ሙያ ስልጠና መስክም ወንድ 8,663 ሴት 4,446 በድምሩ ለ13,109 አንቀሳቃሾች ስልጠና ተሰጥቷል፤ አፈፃፀሙም 54.2% ነው፡፡

በመደበኛውም ፕሮግራም በንግድ ስራ አመራር ወንድ 26,535 ሴት 17,099 በድምሩ 43,634 ተጠቃሚዎች ስልጠና ያገኙ ሲሆን አፈፃፀሙም 75.6% መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

### የምክር አገልግሎት፡

በፓኬጅ ፕሮግራም ታቅፈው ሁሉ አቀፍ ድጋፍ ለሚሰጣቸው 10,800 አባላት የምክር ድጋፍ ለመስጠት ታቅዶ ለ13,481 አንቀሳቃሾች ድጋፍ ሲደረግ በመደበኛ ፕሮግራም ታቅፈው ውስን ድጋፍ ለሚደረግላቸው በንግድ፣ በአገልግሎትና በሌሎች ስራዎች ለተሰማሩ 9,144 አባላት ድጋፍ ለመስጠት ታቅዶ ለ11,614 አባላት የማማከር አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡ በሁለቱም ፕሮግራሞች ክንውኑ ከ100% በላይ እንደሆነ ከውጤቱ መረዳት ይቻላል፡፡

### የመስሪያና የመሸጫ ቦታ አቅርቦት፡

ለተደራጁ አንቀሳቃሾች ከሚሰጡ ድጋፎች መካከል አንዱ የመስሪያና የመሸጫ ቦታ ማዘጋጀትና ማቅረብ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት በበጀት ዓመቱ ዘጠኝ ወራት በክልሉ በፓኬጅ ፕሮግራም ለታቀፉ አንቀሳቃሾች ለግንባታ የሚሆን 80,908 ካሬ ሜትር ቦታ ማመቻቸት የተቻለ ሲሆን በመደበኛ ፕሮግራም ለታቀፉት ደግሞ 103,041 ካሬ ሜትር ቦታ ተመቻችቷል፡፡





*ያለቁ የክላስተር ማዕከላት*

በዚህ ድጋፍ ዙሪያ ያለውን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት በክልሉ ደረጃቸውን የጠበቁና ለማምረቻ አገልግሎት የሚውሉ 309 ብሎክ ህንፃዎች በ22 የከተማ አስተዳደሮች እየተገነቡ ይገኛል፡፡ ግንባታቸውም ሲጠናቀቅ ኢንተርፕራይዞች ተገቢውን ተመጣጣኝ ክፍያ በመፈፀም የሚጠቀሙበት ይሆናል፡፡ በዚህም መሠረት በሀዋሳ፣ በሀላባ፣በሶዶ፣ በይርጋዓለም፣ በአለታወንዶና በዱራሜ ከተሞች ግንባታቸው ተጠናቆ ለርክብክብ ዝግጁ ሆነዋል፡፡ የቀሪ ህንፃዎች ግንባታም በዞን፣ በከተማ አስተዳደርና በማዘጋጃ ቤቶች ርብርብ በቅርቡ እንደሚጠናቀቁ ተረጋግጧል፡፡

## ➢ የፋይናንስ አቅርቦት፡

የክልሉ መንግስት ዜጎች ወደስራ ተሰማርተው ለሀገራቸውና ለራሳቸው ዕድገትን እንዲያመጡ የተቀረፁ ፖሊሲዎችን ወደ መሬት በማውረድ ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል፡፡ በዚሁ መሠረትም ኢንተርፕራይዞችን ለመደገፍ ከሚከናወኑ ተግባራት መካከል ዋንኛው የፋይናንስ አቅርቦት ነው፡፡ በክልሉ የኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት አቅምን ለማሳደግና የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት የብድር ፍላጎትን በከፊል ለማሟላት እንዲቻል የክልሉ መንግስት ከፍተኛ በጀት መድቧል፡፡ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የብድር አገልግሎት እንዲውል በበጀት ዓመቱ 60 ሚሊዮን ብር ፈቅዷል፡፡ ይህንን ብር ለዞኖች፣ ለክፍለ ከተሞች፣ ለወረዳዎችና ለልዩ ወረዳዎች በኤጀንሲው ባለሙያዎች አማካኝነት ተሸንሽኖ በኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም በኩል ለአንቀሳቃሾች እየተሰራጨ ይገኛል፡፡

ከዚህ አንፃር ባለፉት ዘጠኝ ወራት በፓኬጅ ለተደራጁ ተጠቃሚዎች 21,576,399 ብር እንዲሁም በመደበኛ ፕሮግራም ለታቀፉ ተጠቃሚዎች 70,772,121 ብር በድምሩ 92,384,520 ብር ብድር ተሰራጭቷል፡፡ በብድር አመላለስ በኩልም ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከሁለቱም ፕሮግራም ተጠቃሚዎች ብር 66,468,774 ተመላሽ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

- **የገበያ አቅርቦት፡**

የክልሉ መንግስት ኢንተርፕራይዞችን ለመደገፍ ካለው ቁርጠኝነት የተነሳ ተቋማቱ ከሌላ ባለሀብት ጋር ሳይወዳደሩ በመንግስት መስሪያ ቤቶች በኩል የሚፈጠሩ የገበያ ዕድሎችን እንዲጠቀሙ ደንብ አውጥቷል፡፡ በዚሁ የደንብ ቁጥር 60/99 መሠረት ጊዜያዊ የአትኩሮት ቲም ተቋቁሟል፡፡ ቲሙም ሀገራዊና ክልላዊ የገበያ ትስስሮችን ለመፍጠር መርሃ-ግብር አዘጋጅቷል፡፡

በዚህ መርሃ-ግብር መሠረትም ከዩኒቨርሲቲዎች፣ ከኮሌጆች፣ ከሆስፒታሎች፣ ከቴክኒክና ሙያዎች እና ከሴክተር መስሪያ ቤቶች ጋር የመግባቢያ ሰነዶችን በመፈራረምና ከክልሉ ሜይንስትሪሚንግ ቦርድ አባል ቢሮዎች ጋር በመነጋገር ከየቢሮዎቹ ስራውን የሚከታተሉ አንዳንድ ፎካል ፐርሰን እንዲወከል ተደርጓል፡፡በዚሁ መሠረት ኤጀንሲው ከክልሉ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ጋር ከዚህ በፊት በገጠር ቴክኖሎጂ ማዕከላት ይሰሩ የነበሩ በአርሶአደሩ ዘንድ የተለመዱ ቴክኖሎጂዎችን /ዘመናዊ የንብ ቀፎ፣ ዘመናዊ የቆጮ መፋቂያ፣ ዘመናዊ የጫጩት ማሳደጊያ መሳሪያዎች/ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ብቻ እንዲሰሩ ውል ተገብቷል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በክልሉ ባሉ 4 ዩኒቨርስቲዎች፣ 9 ሆስፒታሎች እና 6 ቴክኒክና ሙያ ማሠልጠኛ ተቋማት ውስጥ የሚገኙ ገበያዎችን /የደንብ ልብስ ስፌት፣ እንጀራ መጋገር፣ ካፍቴሪያ፣የኮብል ድንጋይ ንጣፍ፣ የግንባታ ማጠናቀቂያ ስራዎችንና የግቢ ውበትና ፅዳት ስራዎች) ለኢንተርፕራይዞች ለመስጠት ስምምነት ተደርጓል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ከክልል ቢሮዎችም ሆነ ከዩኒቨርስቲዎችና ሆስፒታሎች ጋር የተፈጠሩ የገበያ ዕድል መረጃዎች ለየከተሞቹ ተልኳል፡፡ ገበያውንም ተከታትለው እንዲጠቀሙ ዝርዝር የገበያ ዕቅድ ተዘጋጅቶ እስከ ታችኛው መዋቅር ድረስ እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት በገጠር የሚገኙ
ወጣቶች ከስራ አጥነት ይላቀቃሉ !



**እንጀራ በመጋገር የተደራጁ ሴቶች**
**በተፈጠረላቸው የገበያ ዕድል እየተጠቀሙ ያሉ (ሀዋሳ ዩኒቨርስቲ)**

በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ ዘጠኝ ወራት በፓኬጅ ፕሮግራም ለተደራጁ አባላት የብር 96,888,074 የገበያ ዕድል ሲመቻች በመደበኛው ፕሮግራም ደግሞ የብር 16,105,139 የገበያ ዕድል ተፈጥሮ ከ13 ሺህ በላይ አንቀሳቃሾች ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

➷ **የመረጃ አቅርቦት፡**

ይህን ዘርፍ ለማልማት ከሚደረጉ ድጋፎች አንዱ የመረጃ ድጋፍ ነው፡፡ ይህ ድጋፍ አዋጭ የንግድ መስክ ለመምረጥ፣ የተሻለ የገበያ ዕድል ተጠቃሚ ለመሆን ባጠቃላይ ለኢንተርፕራይዞች ልማት ወሳኝ ከመሆኑ አንፃር ባለፉት ዘጠኝ ወራት ውስጥ ለ55,907 ተጠቃሚዎች የመረጃ ድጋፍ ቀርቧል፡፡ በመደበኛውም ፕሮግራም ለ44,330 ተጠቃሚዎች ይኸው ድጋፍ የተደረገ በመሆኑ የተሻለ ውጤት ተመዝግቧል፡፡

ባጠቃላይ ከላይ የተገለፁትን ድጋፎች በንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ስር በሚገኘው የኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ አማካኝነት በታቀደና በተቀናጀ መልኩ እስከታችኛው መዋቅር ተሰጥቷል፡፡ በመሆኑም በከተሞች አጠቃላይ ለውጥ ታይቷል፡፡

ይሁንና የስራ-አጥ ቁጥር ለመቀነስ በቀጣይም የክልሉ መንግስትና ቢሮው ትኩረት ሰጥተው የሚሰሩ ሲሆን በተሰበሰበው መረጃ መሠረት በክልላችን ከተሞች ወንድ 43,796 ሴት 32,987 በድምሩ 76,783 ስራ-አጦች ተመዝግበዋል፡፡ ለእነኚህም በቀጣይ ወደ ስራ የሚሰማሩበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡ በምዝገባው ያልተካተቱም ሊኖሩ ስለሚችሉ በቀጣይ የሚታይ ይሆናል፡፡

ቢሮው በክልሉ አጠቃላይ ዕድገት ለማምጣት የከተማ ድኅነትንና ስራ-አጥነትን ብቻ መቅረፍ ሳይሆን በክልሉ ገጠር ወረዳ ማዕከላት ያለን ስራ-አጥነትና ድኅነት ለማስወገድ በቀጣይ ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ መጠነ ሰፊና የተደራጀ ስራ ይሰራል፡፡ ስለዚህ በነኚሁ አካባቢዎች የሚገኙ ወጣቶች፣ ሴቶችና ሌሎች ወደ ስራ ተሰማርተው ሀገራቸውንና ራሳቸውን እንዲጠቅሙ ጥረት ይደረጋል፡፡